# በብሔራዊ የአሰሪና

## ሰራተኛ ግንኙነት ሕግ መሰረት የሰራተኛ መብቶች

ብሔራዊ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ሕግ (The National Labor Relations Act/ NLRA) ሰራተኞች የመደረጀት እና ከአሰሪዎቻቸው ጋር በጋራ የመደራደር፣ እና በሌላ የተጠበቁ ተጨባጭ ድርጊቶች የመሳተፍ ወይም ከላይ በተጠቀሱት እንቅስቃሴዎች ላይ በማናቸውም ላይ ላለመሳተፍ ራሳቸውን ለማቀብ ስለመቻል ያላቸውን መብት በተመለከተ ዋስትና ይሰጣል፡፡ በNLRA* ሽፋን ያላቸው ሰራተኞች ከአሰሪ እና የሰራተኛ ማህበር አግባብ ያልሆኑ ባህሪያት የተጠበቁ ናቸው፡፡ ይህ ማስታወቂያ ስለመብትዎ፣ ስለ አሰሪዎች እና የሰራተኛ ማህበራት በNLRA ስር ያለባቸው ግዴታዎችን በተመለከተ አጠቃላይ መረጃ ይሰጥዎታል፡፡ በርሶ የራስዎ የሥራ ቦታን ባህሪ መሰረት ያደረገ ምንም ዓይነት ጥያቄ ካልዎት በNLRA ስር የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ መፍትሄ  የሚሰጠውን የፌደራል ኤጀንሲ ለሆነው ብሔራዊ አሰሪ ሰራተኛ ግንኙነት ቦርድ (National Labor Relations Board/ NLRB) ከዚህ በታች በተሰጠው አድራሻ ተጠቅመው ያግኙት፡፡

### በNLRA ስር፣ የሚከተሉት መብቶች አልዎት፤

- ከአሰሪዎ ጋር ስለደምዎዝዎ፣ የሥራ ሰዓትዎ እና ሌሎች ማናቸውም የሥራ ቅጥር ግዴታዎችና ደንቦችን በተመለከተ በማህበር ተደራጅቶ የመደራደር፡፡.
- የሰራተኛ ማህበር ማቋቋም፣ መቀላቀል ወይም መደገፍ፡፡
- በማህበር ተደራጅቶ ከሌሎች ሰራተኞች ጋር በጋራ ከአሰሪዎ ጋር በሰራተኛው ምርጫ ላይ የተመሰረተ የሥራ ውል በመምረጥ ስለደምዎዝዎ፣ የሥራ ሰዓትዎ እና ሌሎች ማናቸውም የሥራ ሁኔታዎችን መወሰን፡፡
- ደምዎዝዎን፣ ጥቅማጥቅሞችዎን እና ሌሎች የሥራ ቅጥሩን የተመለከቱ ደንቦችና ሁኔታዎችን በተመለከተ እና ማህበርን በተመለከተ ከሥራ ባልደረቦችዎ ጋር ወይም ከማህበርዎ ጋር መወያየት፡፡
- ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ የሥራ ባልደረቦች ጋር በመሆን የሥራ ቦታዎን ሁኔታ ለማሻሻል እንደ ሥራ ነክ የሆኑ አቤቱታዎችን በቀጥታ ለአሰሪዎ ወይም ለመንግስት ኤጀንሲ ማቅረብን እና ከሰራተኛ ማህበር እገዛን መፈለግን የመሳሰሉ እርምጃዎችን መውሰድ፡፡
- በሥራ ማቆም አድማ እና በተቃውሞ መግለጫ ምክንያት እና አግባብ በመመርኮዝ ሥራ ማቆም አድማ ላይ መሳተፍ ወይም ተቃውሞ መግለጽ፡፡
- ሰራተኛ ማህበርን መቀላቀል ሆነ አባል ሆኖ መቀጠልን ጨምሮ ማናቸውንም መሰል እንቅስቃሴዎች ላለመድረግ መምረጥ፡፡

### በNLRA ስር፣ አሰሪዎ የሚከተሉትን ቢያደርግ ሕገወጥ ነው፤

- ከሥራ ሰዓት ውጪ፣ ለምሳሌ ከሥራ በፊት ወይም በኋላ ወይም በእረፍት ጊዜ ስለሰራተኛ ማህበር ማውራት ወይም ማስተባበር እንዳይችሉ ማገድ፣ ወይም የሰራተኛ ማህበር የቅስቀሳ ጽሑፎችን ከሥራ-ሰዓት ውጪ፣ የሥራ ካልሆኑ ቦታዎች ላይ፣ ማለትም እንደ መኪና ማቆሚያ ቦታ ወይም እረፍት ማድረጊያ ክፍሎች ውስጥ እንዳይበትኑ ማገድ፡፡

### NLRA ስር፣ አንድ የሰራተኛ ማህበር ወይም እርሶን የሚወክል የሰራተኛ ማህበር ከርሶ አሰሪ ጋር ሲደራደር የሚከተሉትን ቢያደርግ ሕገወጥ ነው፤

- ለሰራተኛ ማህበር ድጋፍዎን እንዲሰጡ ለማድረግ ማስፈራራት ወይም መዛት፡፡
- የሰራተኛ ማህበር መሪዎችን ስለወቀሱ ወይም የሰራተኛ ማህበር አባል ስላልሆኑ የርሶን አቤቱታ ለማቅረብ አለመስማማት፡፡

- ስለ ሰራተኛ ማህበር ድጋፍዎ ወይም እንቅስቃሴዎ ያንን እንዳያደርጉ በሚያግድ መልኩ ለርሶ ጥያቄ ማቅረብ፡፡
- የሰራተኛ ማህበር አባል ስለሆኑ፣ ወይም ስለደገፉ ወይም በጋራ ለሚገኙ ጥቅሞች እና ድጋፎች እና ጥበቃ መገኘት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ስለተሳተፉ፣ ወይም በነዚህ መሰል ተግባራት ላይ ላለመሳተፍ በመምረጥዎ ምክንያት ከሥራ ማባረር፣ ከሹመት ዝቅ ማድረግ፣ ወይም የሥራ ኃላፊነት ቦታ ዝውውር ማድረግ፣ ወይም የሥራ ሰዓትዎን ወይም የሥራ ምድብ ጊዜዎን መቀነስ፣ ወይም ከባድ እርምጃ በርሶ ላይ መውሰድ፣ ወይም መሰል እርምጃዎችን ስለመውሰድ እርሶን ማስፈራራት፡፡
- ሰራተኞች የሰራተኛ ማህበር እንዲወክላቸው በመምረጣቸው ምክንያት ሥራን ለመዝጋት ማስፈራራት፡፡
- የሰራተኛ ማህበር ድጋፍ ማድረግዎን ለማበረታታት ወይም ለማስቀረት የሥራ ዕድገት፣ የክፍያ ጭማሪ ወይም ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን ለመስጠት ቃል መግባት ወይም መስጠት፡፡
- የሰራተኛ ማህበር ኮፍያዎችን፣ አዝራሮችን፣ ቲ-ሸርቶችን እና ሜዳሊያዎችን በሥራ ቦታ ላይ ልዩ ከሆኑ ሁኔታዎች ውጪ እንዳይለብሱ ወይም እንዳያደርጉ መከልከል፡፡
- ሰላማዊ የሆኑ የሰራተኛ ማህበር እንቅስቃሴዎችን እና ስብሰባዎችን መሰለል ወይም በቪዲዮ መቅዳት ወይም ይህን እንደሚደረግ ማስመሰል፡፡
- ከቀጣሪ ክልል የሥራ ልምድ ምስክርነት በመስጠት ላይ አድሎዋዊ መስፈርቶችን ወይም የአፈጻጸም አካሄዶችን መጠቀም፡፡
- ከሰራተኛ ማህበር ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን እንቅስቃሴዎች በማድረግዎ ወይም በተለመከተ አሰሪ እርሶ ላይ የአድልዎ እርምጃ እንዲወስድ ማድረግ ወይም መገፋፋት፡፡
- የሰራተኛ ማህበሩ አባል ባለመሆንዎ ወይም ባለመደገፍዎ በርሶ ላይ ማናቸውንም ከባድ እርምጃ መውሰድ፡፡

**እርሶ እና የሥራ ባልደረቦችዎ እንደ የናንተ የድርድር ወኪል እንዲሆን የሰራተኛ ማህበርን ከመረጣችሁ፣ አሰሪዎ እና የሰራተኛ ማህበሩ በታማኝነትና በእውነት የተባለውን ድርድር እንዲያካሂዱ በዚህም  የሥራ ቅጥሩን ሁኔታ እና ደንቦች ገዢ ሁኔታዎች በማስቀመጥ ላይ ሐቀኛ በሆነ መንገድ የጽሑፍ ስምምነት ላይ እንዲደርሱ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሰራተኛ ማህበሩ ስምምነቱን በመደራደር እና በማስፈጸም ላይ እርሶን በአግባቡ ሊወክልዎት ይገባል፡፡**

**ሕገወጥ ባህሪ አይፈቀድም፡፡** የርስዎ መብት ወይም የሌሎች መብት ተጥሷል ብለው የሚያምኑ ከሆነ በአስቸኳይ መብትዎን ለማስጠበቅ ሕገወጥ ድርጊቱ በተፈጸመ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ለNLRB ማሳወቅ አለብዎት፡፡ ስለተፈጸመ የመብት ጥሰት አሰሪዎ ሆነ ሌላ ማንም አካል ሳይሰማ ማጣራት እንዲደረግ ለመጠየቅ ይችላሉ፡፡ ክሶች በማንም ሰው ሊመሰረቱ የሚችሉ ሲሆን የግድ የመብት ጥሰት በተፈጸመበት ሰራተኛ አማካኝነት መቅረብ የለባቸውም፡፡ NLRB ሕግን በጣሰ መልኩ የተባረረ ሰራተኛን አሰሪ መልሶ እንዲቀጥር ወይም ያልተከፈሉ መከፈል የነበረባቸውን የደምዎዝ እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች ክፍያ እንዲከፍል ሊጠይቅ እንዲሁም አሰሪን ወይም የሰራተኛ ማህበርን ሕግ መጣሱን እንዲያቆም ሊያዝ ይችላል፡፡ ሰራተኞች በአቅራቢያቸው ከሚገኝ የ ቢሮ ድጋፍ መጠየቅ አለባቸው፣ አድራሻዎቹን ከኤጀንሲው የድርጣቢያ፤ http://www.nlrb.gov ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡

እንዲሁም NLRB በሚከተለው ስልክ ቁጥር በመደወል ማግኘት ይችላሉ፤ ነጻ የስልክ መስመር፤ **1-866-667-NLRB (6572)** ወይም መስማት ለተሳናቸው በነጻ የስልክ መስመር **(TTY) 1-866-315-NLRB (1-866-315-6572)**፡፡

If you do not speak or understand English well, you may obtain a translation of this notice from the NLRB's Web site or by calling the toll-free numbers listed above.

---

*ብሔራዊ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ሕግ (National Labor Relations Act) አብዛኛዎቹን የግሉ-ዘርፍ አሰሪዎችን ያጠቃልላል፡፡ የሕዝብ-ዘርፍ ሰራተኞች፣ የእርሻ እና የቤት ውስጥ ሰራተኞች፣ ራሳቸውን የቻሉ ሥራ ተቋራጮች፣ በወላጅ ወይም የትዳር ጓደኛ የተቀጠሩ ሰራተኞች፣ የአየር ወይም የባቡር ማጓጓዣ ሰራተኞች እና ተቆጣጣሪዎች (ምንም እንኳን ተቆጣጣሪዎች የ ሕግ በሚጥሱ ተግባራት ላይ ላለመሳተፍ በመቃወማቸው መድልዎ የደረሰባቸው ሽፋን የሚሰጣቸው ቢሆንም) በNLRA ስር የማይከተቱ ናቸው፡፡

**ይህ የመንግስት ኦፊሲልያዊ ማስታወቂያ ነው በመሆንም በማንም አካል ሊዛባ አይገባም፡፡"**

AMHARIC
OCTOBER 2011